OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# 2025 የከተማ አርቲስት (CityArtist) መመሪያዎች

## የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ አጠቃላይ እይታ

የCityArtist የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ሲያትል በምርምር ውስጥ ያሉ ግለሰብ አርቲስቶችን/ የሙዚየም ሃላፊዎችን፣ በፈጠራ ፕሮጀክት ልማት፣ እና አቅርቦት ላይ የተሰማሩትን ይደግፋል። የ2025 ማመልከቻ **በዳንስ፣ ሙዚቃ፣ እና ቲያትር (የቲያትር ፅሁፍን ጨምሮ)** ውስጥ ለሚሰሩ አርቲስቶች/ተቆጣጣሪዎች ክፍት ነው። የድጋፍ ስጦታውን የተሸለሙ አርቲስቶች በሲያትል ከተማ ክልሎች ውስጥ ለህዝብ አቅርቦት ማድረግ አለባቸው።

ከCityArtist በባህላዊው ዘርፍ እምብርት የሆኑትን አርቲስቶችን፣ አድራጊዎችን እና የሙዚየም ሃላፊዎችን ይደግፋል። ለፈጠራ ስራ ፈጣሪዎች የገንዘብ ድጋፍ መስጠት በከተማው ሁሉ ውስጥ ላሉ ሰፈሮች ሰፊ ኢኮኖሚ እና የህይወት ጥራት አስተዋፅኦ ያደርጋል።

**ለማመልከቻው፣ ብቁነት ወይም ቴክኒካዊ የመስመር ላይ ድጋፍ መረጃ እና እገዛ:** የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ፣ አይሪን ጎሜዝ (Irene Gómez)ን በ (206) 684-7310 ወይም irene.gomez@seattle.gov **ያግኙ።**

**በቪዲዮ የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን ጨምሮ በእርስዎ ቋንቋ መናገር የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** ይደውሉልን እና ምን ቋንቋ እንደሚናገሩ ይንገሩን። ሲደውሉ አስተርጓሚ ስናፈላልግ እስከሚቀላቀለን ለአጭር ጊዜ ቆም ብለው ይጠብቁ።

| | |
|---|---|
| **ማመልከቻ**<br>ማመልከቻው የሚገባው በመስመር ላይ (ONLINE) ነው። ማመልከቻው የሚገኘው በሲያትል ከተማ የድጋፍ ስጦታ ድህረ ገጽ መግቢያ በኩል በFLUXX ላይ በ https://seattle.fluxx.io/user_sessions/newነው<br><br>የኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት መድረሻ ከሌለዎት በተቻለ ፍጥነት አይሪን ጎሜዝን በ (206) 684-7310 ያግኙ። | **የሚከፈተው**<br>ማክሰኞ፣ ሚያዝያ 2 ቀን 2024፣ ጥዋት 8 (ፓስፊክ)<br><br>**የማስረከቢያ ዕለተ ቀን**<br>ማክሰኞ፣ ግንቦት 7 ቀን 2024፣ ከምሽቱ 5 ሰዓት (ፓስፊክ) |
| **ምናባዊ የመረጃ ክፍለ-ጊዜዎች:-**<br><br>**ክፍለ ጊዜ 1**<br>ሰኞ፣ ሚያዝያ 8፣ ከሰዓት ከ3 - 5 (ፓሲፊክ):-**እባክዎን መልስ ይስጡ (RSVP)**<br><br>**ክፍለ ጊዜ 2**<br>እሮብ፣ ሚያዝያ 17፣ ከሰዓት ከ1 - 3 (ፓስፊክ):- **RSVP** | **20-ደቂቃ 1:1 የስልክ ረቂቅ ግምገማዎች**<br>ሰኞ፣ ሚያዝያ 22 እና 29፣ ከሰዓት ከ1 - 5 (ፓስፊክ)<br><br>እባክዎን መልስ ለመስጠት፣ **የቀን መቁጠሪያችንን ይጎብኙ** እና ሚያዝያ 22 ወይም ሚያዝያ 29 ላይ የመረጡትን የጊዜ ሰሌዳ ይምረጡ።<br><br>**እንዲሁም ደግሞ መመሪያዎቹ በቻይንኛ (ባህላዊ)፣ አማርኛ፣ ኮሪይኛ፣ ሶማሊኛ፣ ስፓኒሽ፣ ታጋሎግ እና በቬትናምኛ ይገኛሉ።** |

**ስልክ ክፍት የሆኑባቸው የቢሮ ሰዓቶች:-**

እሮብ፣ ከመጋቢት 27 - ሚያዝያ 24፣ ከሰዓት ከ3 - 5

(ፓስፊክ)

## የብቁነት/ መስፈርቶች

እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ ለዚህ የድጋፍ ስጦታ ብቁ ነዎት:-

- እርስዎ ኪነ ጥበብ የሚያዘጋጁ /የሚያቀርቡ አርቲስት/ የሙዚየም ሃላፊ ነዎት።
- እርስዎ የሲያትል ነዋሪ ነዎት ወይም መላላኪያ ፖስታ ለእርስዎ የሚደርስበት ቦታ ሲያትል ከተማ ገደብ ውስጥ ቋሚ ስቱዲዮ/የመስሪያ ቦታ አለዎት። የፖስታ ቤት ሳጥን* ሊሆን **አይችልም**።
- በማመልከቻው ማስገቢያ እለተ ቀን ዕድሜዎ ቢያንስ 18 አመት ነው።
- እርስዎ ግለሰብ አርቲስት/ የሙዚየም ሃላፊ ወይም የአርቲስቶች/ የሙዚየም ሃላፊዎች ቡድን መሪ አርቲስት ነዎት።
- የኪነጥበብ ወይም የባህል ቡድን/ድርጅት መሪ አርቲስት/ ሃላፊ ከሆንክ፣ለዚህ ሽልማት ስራ አሁን እየተካሄደ ካለው ቀጣይ/ወቅታዊ ስራ ከእርስዎ ከቡድን/ ከድርጅት ሥራ በግልፅ መለየት ይኖርብዎታል።

ለዚህ ስጦታ ብቁ አይደሉም ከሆነ:-

- ከራስ ጥበባዊ ስራ ወይም የሙያ ተግባር ጋር በተገናኘ በማንኛውም የዲግሪ መርሃ ግብር በማንኛውም ደረጃ (የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ምሩቅ ወይም ዶክትሬት ዲግሪ) ትምህርት ቤት ተመዝግበዋል፤
- በማንኛውም የኪነጥበብ እና የባህል ቢሮ ፕሮግራም አሁን ገቢር ውል ጋር የአሁኑ ሽልማት ተቀባይ ነዎት።

## የገንዘብ ድጋፍ

ሽልማቶች **ለሁሉም** ተቀባዮች በአንድ ነጠላ መጠን $8,000 ዶላር ተዘጋጅቷል። የሥራው ወሰን እና የመጨረሻው ክስተት ዝርዝሮች የሚወሰኑት የሽልማቶች ኦፊሴላዊ እና ውሉ የሚከናወንበት ደረጃ ወቅት **ከሆኑ በኋላ** ነው።

## የግምገማ መስፈርቶች

የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳቦች የሚገመገሙት በሶስት (3) መመዘኛዎች መሰረት ነው። አመልካቾች በማመልከቻ ማቴሪያሎቻቸው ውስጥ ለእነዚህ መስፈርቶች ምላሽ እንዲሰጡ ይበረታታሉ። ባንድነት በድምሩ 60 ነጥቦች የሚገመገም፣ ከታች ያለው እያንዳንዱ መስፈርት በየግሉ 20 ነጥብ ሊያወጣ የሚችሉ ውጤት አለው።

**ልምድ እና ራዕይ (20 ነጥቦች)**

- ከአሁኑ ሥራ ጋር ሲወዳደር መን እንዳነሳሳው፣ ተጽዕኖ ያሳደረውን ወይም ካለፈው ድፍረት ሃሳብ ወይም ጭብጥ ያስቀረጸውን ሥራ ያካፍላል።
- አርቲስት/ የሙዚየም ሃላፊ ለቀጣይ ጭብጥ ወይም ርዕስ እንዴት እንደሚማር ወይም እንደሚዘጋጅ ይገልጻል።

**እድገት እና እምቅ አቅም (20 ነጥቦች)**

- በጊዜ ሂደት የኪነ ጥበባዊ እድገትን፣ ስልጠናን ወይም ስራን እንደ አርቲስት/ የሙዚየም ሃላፊ ይገልጻል።
- ችሎታዎችን ወይም አካሄዶችን (ልምምዶችን፣ ችሎታዎችን ወይም ስልቶችን) ለማጠናከር ምን እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ያሳያል።

**የስራ ናሙና (20 ነጥብ)**

- *የሥራ ናሙናዎች የትምህርት/ የሥራ ልምድ ታሪክን፣ የትርክት ምላሾችን፣ የእጅ ሙያ ደረጃን ወይም ቀጣዩን ፈለግ እንዴት እንደሚያንጸባርቁ ያሳያል።*
- *ናሙናዎች የሚነበቡ፣ የሚሰሙት፣ የሚታዩ እና ተደራሽነት ያላቸው ናቸው።*

## የማመልከቻ ይዘቶች

የሲያትል ከተማ FLUXX የተሰኘ የመስመር ላይ ማመልከቻ ሥርዓት እየተጠቀመች ነው። አመልካቾች ማመልከቻውን መጠቀም ከመጀመራቸው በፊት፣ ቀደም ሲል ከሌላቸው፣ የሂሳብ መለያ እና ስለራሳቸው መግለጫ በፊት መፍጠር አለባቸው።

- የእርስዎን መነሳሳት እና ተሞክሮዎችን የሚገልጹ ሁለት (2) የትረካ ጥያቄዎች ያለፉትን እና የወደፊት ሀሳቦችን ወይም ስራዎች። እነዚህ ከፕሮጀክት ወደ ፕሮጀክት እንዴት እንደሚዳብሩ የሚናገሩ።
- የሥልጠና፣ የትምህርት፣ ከንውኖች፣ እና ስኬቶች (ክስተቶች፣ ማስተማር፣ ንግግሮች፣ የመኖሪያ ቦታ፣ መጣጥፎች፣ ወዘተ) ታሪክን የሚዘረዝር እንደ ለሥራ ለማመልከት የትምህርት/ የሥራ ልምድ ታሪክ
- የአርቲስት አመልካች ስራን የሚያሳይ እና ትረካ የሚደግፍ እና የትምህርት/ የሥራ ልምድ ታሪክን የሚያሳይ የስራ ናሙና።